# BERUH ETHIOPIA DEMOCRATIC MOVEMENT

## ብሩህ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ

- **email:**BeruhBeruh2@gmail.com
- **website:** http://www.beruh.org/


Sept 18, 2018

### **በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከብሩህ** ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተሠጠ መግለጫ

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያው የታየው አለመግባባትና ግጭት የበርካታ ወገኖቻችንን ሕይወት የነጠቀ፤የአካል ጉዳት ያደረሰና ንብረት ያወደመ እንዲሁም ዜጋዎቻችንን ከቤት ንብረታቸው ያፈናቀል  አሳዛኝ አደጋ በመሆኑ የብሩህ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልጻል።

እንዲህ ዐይነቱ አስደንጋጭና አሳፋሪ ድርጊት በጽኑ መኮነንና መወግዝ አለበት። መንግስትም  የወንጀሉ መንሰዔ  ግልጽነት በተላበሰ መንገድ አጣርቶ ወንጀለኞችን ለፍርድ የማቅረብ ሀላፊነትና ግዴታ አለበት። ሀገርና የሀገር ልማት  ሊያድግና ትክክለኛውን አቅጣጫ ሊይዝ የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ የዜጎች ሙሉ መብት ተጠብቆ በመርጡት ስፍራ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ያለምንም ሥጋት ደህንነታቸው ተጠብቆ መስራትና መኖር እንደሚችሉ በመንግስት በኩል በተደጋጋሚ ቢነገርም በተገባር ላለመዋሉ የሰሞኑ ክስተት በቂ ማሰረጃ ነው።

በእኛ ዕምነት ይህንን መሰረታዊ የዜግነት መብት ዋስትና ያሳጣው፤ ሀገራችንን በጎሳ ሸንሽኖ የማደራጀቱ አባዜ በመሆኑ ይህ በታኝ የአደረጃጀት ዘይቤ ሕገ መንግስታዊ ማዕቀፍ ተሰጥቶት ሙሉ በሙሉ መገታትና በህግ መታገድ እንዳለበት እናምናለን። ይህ የአደረጃጀት ልምድ መፍትሄ ካላገኘ ከዚህ የባሰ ብጥብጥና ዕልቂት ውስጥ ሊከተን ስለሚችል አገሬ ኢትዮጵያን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ የችግሩን አሳሳቢነት በአንክሮ በማጤን  በጎሳ የመደራጀትን የማደራጀት ሂደት  በህግ እንዲታገድ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!
አንድ አገር ኢትዮጵያ፤ አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ!!!